FRIEDRICH EBERT STIFTUNG




# ሰራተኞችን እናብቃ

# የአቅም ግባቶች ስብስብ ፡ 2024

የቅጂ መብት © FES ኢትዮጵያ መብቱ በህግ
የተጠበቀ ነው።

የግንኙነት ስትራቴጂ በ፡ Unbox Marketing
www.unbox-marketing.com

ማሳያ/ማብራሪያዎች በአለማየሁ ተፈራ
(አሌክስ) 2024 Teferaalex4@gmail.com

በእያንዳንዱ ስኬታማ እና ጥሩ የስራ ቦታ ውስጥ የማይካድ የሰራተኞች አቅም፣ የተደረጁ ሰራተኞች ፣ ፍትሃዊ አሰራሮች እና ትርጉም አዘል እድገት አለ።

ይህ የአቅም ግባቶች ይፈጥራሉ በየቦታው - በተለይም በኢትዮጵያ ያሉ ሰራተኞች የጋራ አቅማቸውን ለመጠቀም እና ወደ ውጤታማ ተግባር ለመሸጋገር ይችሉ ዘንድ እንደማሳየ የተዘጋጀ ነው። ለዚህም እንደ ሀረግ፣ ገመቺስ፣ ቢኒያም እና ሀያት ባሉ ግለሰቦች አስተማሪ ታሪክ አማካኝነት ሰራተኞች ያላቸውን የተለያዩ የአቅም ዓይነቶች እና ይህን አቅም እንዴት ለለውጥ ማንቀሳቀስ እንደሚችሉ እናሳያለን።

ይህ የአቅም ግባቶች ይፈጥራሉ የተሻለ የስራ ውል ስምምነት ለመደራደር፣ ማኅበረሰብን ለማነሳሳት ወይንም በስትራቴጂካዊ ተግባራት ለመሳተፍ አቅም የሚሆኑ ግንዛቤዎችና ስልቶችን ያቀርባል። የተዘረዘሩት ግንዛቤዎች ከግብአትም በላይ ስርነቀል ለውጥን ለማምጣት በውስጣዊና በአካባቢ ላይ ያለውን እምቅ አቅም እንድንጠቀም ዘንድ ተነሳሽነትን ይፈጥራል።

እውቀትን ታጥቀን፣ በአብሮነት እና በቁርጠኝነት ለውጥ ለማምጣት ይሄን የአቅም ግባቶች ይፈጥራሉ በሚገባ እናጢን።

FRIEDRICH
EBERT
STIFTUNG

# ሀረግን ተዋወቋት፤

የ IT ስፔሻሊስትና በራይድ ታክሲ ድርጅት ውስጥ የእለት ተእለት ስራዎችን በበላይነት የምትከታተል ናት። መዋቅራዊ ኀይሏ ያለው በስራ ቦታዋ እና በገበያው ውስጥ ባላት ድንቅ ብቃትና ልዩ ክህሎት ሚናዋ ውስጥ ነው። ይህ አቅሟ የተሻለ የሥራ ሁኔታዎችን እንድትጠይቅ አስችሏታል።



ሃገራዊ ተደራሽነት
የታክሲ መጥሪያ መተግበሪያ
የሰራተኞች መብት፡
የታክሲ መጥሪያ መተግበሪያ
IXAT
TAXI

FRIEDRICH
EBERT
STIFTUNG

# ገመቺስን ተዋወቁት፤

ገመቺስ በጠርሙስ ፋብሪካ ውስጥ የማሽጊያ ባለሙያ ነው።
ገመቺስ እና ባልደረቦቹ በስራ ቦታቸው ለመብቶቻቸው እና ለተሻለ
ሁኔታዎች በጋራ ለመታገል በአንድነት ቆመዋል።



FRIEDRICH EBERT STIFTUNG

# ቢኒያምን ተዋወቁት፤

የአበባ እርሻ ሰራተኛ የሆነው ቢኒያም፣ ከአካባቢ ማኅበረሰቦችን በማስተሳሰር ረገድ ጎበዝ ነው። ለሠራተኛ ማኅበሩ ድጋፍ ለማግኘት እና  የተሻለ የስራ ሁኔታ ለመጠየቅ ከሌሎች ማኅበራዊ ቡድኖች ጋር በትብብር መስራት መቻሉ ማህበራዊ ተፅእኖ አስገኝቶታል።


ማኅብበር ከሌለ ፍትህም የለም።
የሰራተኞች ድል፡ የኅብረተሰብ እድገት
ህብረት የበለጠ ጠንካራ ያደርገናል
ማኅበር ከሌለ ፍትህም የለም።
ዳቦ እንፈልጋለን ፅጌረዳዎችም እንዲሁ
ህብረት የበለጠ ጠንካራ ያደርገናል

FRIEDRICH EBERT STIFTUNG

# ሀያትን ተዋወቋት፤

የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ሰራተኛ እና የማኅበር አባል የሆነችው ሀያት ከዚህ ቀደም ልዩ መብቶችን ለማግኘት የሰራተኛ ማኅበሩን ተጠቅማለች። እንደ ፍርድ ቤቶች ባሉ ጠንካራ ሕጋዊ ማዕቀፋት ድጋፍና በተዘረጋው የጋራ ድርድር ሥርዓት፣ ተቋማዊ ሥልጣኗን በሚገባ አረጋግጣለች።


የተሻሻለ የሰራተኞች
መብት ሰነድ

FRIEDRICH
EBERT
STIFTUNG

# የአቅም ሀብቶችዎ ምንድን ናቸው?
# እነሱንም ለማግኘት ይሞክሩ!

# የSWOT ትንተና

ገመቺስ እና የስራ ባልደረቦቹ የጋራ አቅማቸውን ለመጠቀም ያላቸውን ጥንካሬ፣ድክመቶች፣እድሎች እና ስጋቶች ይገመግማሉ። የቀጣሪያቸው ዕጣ ፈንታ በሰራተኞቹ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ይገነዘባሉ!



እኛም ሰዎች
የሰራተኞች መብቶች
በጋራ እንቆማለን
የሰራተኞች መብቶች
የሰራተኞች መብቶች
በጋራ እንቆማለን
እኛም ሰዎች ነን
የሰራተኞች መብቶች
በጋራ እንቆማለን

FRIEDRICH EBERT STIFTUNG

# መሰናክሎችን መስበር

ሀያት የሥርዓተ-ፆታ ውክልናን በተመለከተ ትሟገታለች። በሥዕሉ ላይ እንደሚታየው የሥርዓተ-ፆታን ውክልና በተመለከተ እድገትን የሚገታ የስርዓት ተግዳሮቶች ገጥሟታል። እነዚህን ተግዳሮቶች ለማስተካከል ቀጥተኛ እርምጃ መውሰድን ትደግፋለች።


የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ

FRIEDRICH
EBERT
STIFTUNG

# ስትራቴጂካዊ የድርጊት መርሃ ግብር

ወደፊት ለመራመድ እና የሰራተኛ ማኅበራትን የአመራር እና የንቅናቄ ጥረቶች ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ተጨባጭ አላማዎችን በግልፅ መነሻ ነጥብ ማኖር ወሳኝ መሆኑን ሀረግ ትገነዘባለች።


ምቹ የስራ ሁኔታዎች? እንዴት?
የሰራተኞች ጥያቄ!
ለዓለም ?
አምስታችን ብቻ ?

FRIEDRICH
EBERT
STIFTUNG

# በይነ መረቦች

ቢኒያም በስራ ቦታው አስፈላጊ ሰነዶችን ለማግኘት እንቅፋት ስለገጠመው በሰራተኞች መካከል ጠንካራ የግንኙነት መረቦችን አስፈላጊነት ይገነዘባል። ይህ ድጋፍ የጋራ እንቅስቃሴያቸውን እና ተግባራቸውን ለማራመድ ወሳኝ ነው።


ደብዳቤያችን ደርሶሃል?
አዎ፡ ግን ፊርማው በደንብ አይታይም
የአበባ እርሻ ሰራተኞች ማግኘት የሚገባቸውን ደመዎዝ በተመለከተ መረጃ አለን?
አይ .. መረጃ ለማግኘት አልተቻለም ነበር
የስብሰባውን ሰዓት አሳውቀሃቸዋል ?
ውይ፡ እረሳሁት።

FRIEDRICH
EBERT
STIFTUNG

# ቅድሚያ መስጠትና እና ክትትል

ቅሬታ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው በኩራት ስሜት ይቀርባል። ሆኖም፣ ቅሬታ ከማስገባት የለፈ ነገር የለውም ፣ ምክንያቱም ብዙ ቅሬታዎች ወደ ጎን ይገፋና ተግባራዊ ሳይሆኑ ይቀራሉ። እውነተኛ ስኬት ቀጣይነት የለው ክትትልና ተጨባጭ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ማረጋገጥ ነው።


ለዛሬ ስራዬ ተጠናቅቋል
ቅሬታዎች

FRIEDRICH
EBERT
STIFTUNG


# የቅስቀሳ መልእክት

ሃያት በአጭር፣ አሳማኝ እና አነቃቂ የቅስቀሳ መልዕክቶች ውጤታማ ናት። ከረዥም እና ግልጽ ካልሆኑ መልዕክቶች በተለየ መልኩ አጫጭር እና ማራኪ መልዕክቶች የሰራተኛው ጥያቄ በአግባቡ እንደሚያስተላልፍና እና ሰፊ የማኅበረሰብ ድጋፍን እንደሚያሰባስብ ትገነዘባለች።


TEXTILE COMPANY
ደመወዝ ተመጣጣኝ መሆን አለበት!
ደመወዝ ተመጣጣኝ
መሆን
ደመወዝ ተመጣጣኝ መሆን አለበት!
እኩልነት ለሁሉም!
የፆታ እኩልነት!
የሴቶች ተሳትፎ በአስተዳደራዊ ምህዳር!

# የካርታ ሰንጠረዥ

ቢኒያም ለሰራተኞች ጉዳይ ቁልፍ ተዋናዮችን እና አጋሮችን ለመለየት የስራ ቦታውን ስነ-ምህዳር ካርታ ያዘጋጃል። ሊለውጠው ያሰበውን ስርዓት ከውጫዊ ተጽእኖዎች ጋር መረዳቱ ውጤታማ ስትራቴጂ ለመቅረጽ አስፈላጊ መሆኑን አምኗል።


ባንክ
NGO
መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት
የሰራተኛ ማህበር
የህዝብ ማህበር

FRIEDRICH
EBERT
STIFTUNG

# ስትራቴጂ እና የሰራተኛ ዘዴዎች

ገመቺስ እና ባልደረቦቹ የድርጅቱን ወቅታዊ ሁኔታ እና ሰፊ ስነ-ምህዳር በመረዳት ለድርድር ይዘጋጃሉ። ይህ ውጤታማ መረጃ ከአሠሪው የሚደርስባቸውን ጫና ለመቋቋም የሚያስችላቸውን ዕውቀት ያስጎናጽፋቸዋል።


ኑ ቡና
ጠጡ
የሰራተኛ ፍላጎት
10 በ100 የደመወዝ ጭማሪ
የተሻሻለ የስራ ሁኔታ
ሰራተኞችን የሚያጋጥሙ ፈተናዎች
ምርት በ20 በ100 መቀነስ
ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ
አዲስ ተወዳዳሪ ወደ ገበያ መግባት

FRIEDRICH EBERT STIFTUNG

# የህብረት ስምምነት ድርድር

ሀያት እና ባልደረቦቿ ለውል ድርድር ከኩባንያው ጋር ይገናኛሉ። ስለ ኩባንያው አሠራር እና የኢንዱስትሪ ሁኔታ በሚገባ የተገነዘበ የሠራተኛ ማኅበር ውጤታማ የጋራ ድርድር ለማድረግ የተሻለ ቦታ እንዳለው ይገነዘባሉ።


ህገመንግስታዊ መብት2022
የስርዓተ ፆታ ዘገባ
የሴቶች መብት

FRIEDRICH EBERT STIFTUNG

# የመደራደሪያ ነጥቦች

እንደ ሰራተኛ ተወካይ፣ ቢኒያም ወሳኙ የሰራተኛ ነጥቦችን በደረጃ ያስቀምጣል። ሁለቱም የኩባንያ እና የሰራተኛ ማኅበራት ተወካዮች ድርድሩ ብዙ ጉዳዮችን እንደሚያካትት ይገነዘባሉ። ስለዚህ ግልጽ ውይይቶች በኩባንያው እና በሠራተኛ ማኅበራት መካከል ፍትሃዊ ስምምነት ላይ ለመድረስ ቁልፍ ናቸው።


ጥሩ ክፍያ
ጤና እና ደህንነት
ጥሩ የስራ ቦታ
ኢንቨስትመንት
የኩባንያ ትርፍ
ምርታማነት
የሰራተኞች መብት
ተመጣጣኝ ክፍያ

FRIEDRICH EBERT STIFTUNG

# ድርድሮችን ማሸነፍያ

ሀረግ የአካባቢውን ማኅበረሰብ አባላትን፣ አመራሮችን፣ የሲቪል ማኅበራትን እና የሰራተኛ ማኅበራትን በማሰባሰብ የተሳካ ድርድር እንዲካሄድ ታደርጋለች ። የእሷ ጥረት በኩባንያው እና በመንግስት ደረጃ ውሳኔ ሰጪዎች ላይ ጫና ለመፍጠር ያለመ በመሆኑ፣ የሰራተኞች ፍላጎቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል።



FRIEDRICH EBERT STIFTUNG

# አድማ መምቻ ስልቶች

ገመቺስ እና ባልደረቦቹ የጋራ ኃይላቸውን አረጋግጠዋል። ሌሎች የተሳትፎ ቅጾች ችላ በሚባሉበት ጊዜ የሥራ ማቆም አድማን እንደ ስትራቴጂካዊ አማራጭ በመቁጠር ኩባንየውን ለመቃወም ዓላማ ያደርጋሉ፣ ዓላማቸው የኩባንየውን መሪዎች የሠራተኞችን ስጋት እንዲገነዘቡ ለማድረግ ነው።



FRIEDRICH EBERT STIFTUNG

# የሥራ ውል ረቂቅ ንድፍ ማዘጋጀት

እንደ ሰራተኛ ተወካይ ገመቺስ በኮንትራት ረቂቅ ንድፍ ዝግጅት ውስጥ ግልጽ ቃላቶችን የመጠቀምን አስፈላጊነት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ይህ ግልጽነት እነዚያ መብቶች ፣ የማስረከቢያ ቀናት እና ሌሎች ዝርዝሮች ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ መገለጹን ስለሚያረጋግጥ፣ ለሁሉም ወገኖች ውክልና እንዲሰጥ እና በማንኛውም ቡድን ላይ የሚደርስ መድልዎን ያስወግዳል።


የመግባብያ ስምምነት
የኮንትራት ፕሮፖዛል

FRIEDRICH EBERT STIFTUNG

# የራስዎን የአቅም ግባቶች ለይተው ያውቃሉ?

FRIEDRICH
EBERT
STIFTUNG